# አጠቃላይ ትምህርታዊ መርሀ ግብሮችንና አገልግሎቶችን ለመደገፍ የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶችን እንደገና ማደራጀት

**ኅዳር 13፣ 2007**

የ Brookings ተቋም የጥናት ቡድን፣ የከተማ ተቋም ማለትም የ Urban Institute እና የ 21st Century School Fund ቡድን፣ ከዲሲፒኤስ ቻንስለር Michelle Rhee፣ ከትምህርት ምክትል ከንቲባው Victor Reinoso እና ከስቴቱ የትምህርት ምክትል ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ Deborah Gist ጋር በመተባበር፣ በዲሲ ፒኤስ ትምህርት ቤቶች ተመዝግበው ስለሚገኙ ተማሪዎች ብዛት አዝማሚያ፣ ስለ መኖሪያዎች ክልል መለዋ ወጥ፣ ስለዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች አካላዬች፣ ስለ ትምህርት ቤቶች እዝማሚያ፣ ስለ ቦታ አመዳደብ፣ ስለ ክፍሎች መጨመር ወይም አከፋፈት፣ ስለ ትምህርት ቤቶች መጠንም በተመለከተ እንዴት መደራጀት እን ደሚገባቸው ለመወሰን የሚያስችል ትንተና አበርክተዋል። ይህ ሠነድ ስለ ትምህርት ቤቶች እንደገና መልሶ ሰለ ማደራጀት ሕዝቡ ስለሚያካሂደው ውይይት የመነጋገሪያና ውሳኔም ላይ ለመድረስ የሚያስችል የመንደርደሪያ ቢጋሮችን ይነድፋል።

## መልሶ የማደራጀት አስፈላጊነት

ከ 2000 ጀምሮ የዲስትሪክቱ ጠቅላላ ሕዝብ ብዛት በመጠኑ የጨመረ ቢሆንም ከዚህ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ የልጆች ቁጥር በተዛማጅነቱ ጨምሮ አይገኝም። በ 1967 ከፍተኛ ከነበረው 146,000 ተማሪዎች ቁጥር፣ ባጠቃላይ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ብዛት ያለማቋረጥ እያሽቆለቆለ ነው። በዚህ የተነሣ በአለፍት 10 ዓመታት በዲሲፒኤስ የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር በሚያስገርም ሁኔታ እየቀነሰ መጓዙ እየተባባሰበት ሄዷል። ይህ ማሽቆልቆል እየጨመረ በመሄድ ላይ ከሚገኘው የትምህርት ቤቶች አቅርቦት ጋር በመዳመር ከ 1998 ጀምሮ ዲሲፒኤስ ከ 10 የሚያንሱ ትምህርት ቤቶችን ሲዘጋ በአንፃሩ 70 አዲስ የቻርተር ትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢዎች በመከፈታቸውና ከቀጠና 3 በስተቀር (የድጋፍ ማስረጃውን ይመልከቱ) በየቀጠናው ከፍተኛ ቁጥር ባለው በሕዝብ ትምህርት ቤት መማሪያ ቅጥር ግቢዎችና ድርጅቶች ዲሲፒኤስ የተትረፈረፈ እንዲሆን አድርጎታል። ከሚገባው በታች በዝቅተኛ ደረጃ በመንቀሳቀስ ላይ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ ዲሲፒኤስ አስተዳደሩን የመምራት፣ መምህራንና ሠራተኞችን ማስተዳደር፣ እና ፋሲሊቲዎችንም በሚገባ መቆጣጠር አለመቻል፣ የተሟላ ጥራት ያለው ተጨማሪ የሥራዓተ ትምህርት መርሀ ግብሮች፣ ግልጋሎቶችና የትምህርት እድሎች ለተማሪዎች ሁሉ የመስጠቱን ሁኔታ ውሱን ያደርገዋል። እነዚህ ጉዳዩች በዲሲፒኤስ ዋና የትምህርት እቅድ ላይ (የካቲት 2006) በምዕራፍ VI የተማሪዎችን ፍላጎቶችን በተሻለ ለማሟላት ትምህርት ቤቶችን ማደራጀት፣ እንዲሁም በምዕራፍ VIII እያንዳንዱ ልጅ ተገቢ ይሆኑ በርካታ የትምህርት ሪሶርሶች ማግኘት የሚችል ለመሆኑ እርግጠኛ ስለ መሆን ተብራርተው ነበር። ከሰፊ ትምህርታዊ እቅድ ሂደት በኃላ፣ በ 2006 ላይ የትምህርት ዋና እቅድ መደምደሚያ ተደርጎ ነበር። ይህ ሠነድ የእቅዱ ራእይ ተግባራዊነትና ተፈጻሚነት እንዲሁም ወደ መፍትሔ ሀሳቦች ማድረሻ ቀጣይ እርምጃ ነው።

የዲሲፒኤስ የ 2006 የትምህርት ፍሲሊቲ ዋና እቅድ ሊዘጉ የሚገባቸውን በርካታ ትምህርት ቤቶችን ለይቶ እስቅምጧል። ሆኖም የፊሲሊቲ ዋና ዐቢይ እቅድ፣ ስለ ቦታና ስለ ትምህርት ቤት አመዳደብ፣ ስለ ክፍሎች አወቃቀር፣ ተማሪዎችን ሳኪና መጋቢ ትምህርት ቤቶች ወይም የተማሪዎችን አመዳደብ፣ ጉዳዩችን አይመለከትም። የጥናቱ ቡድን አሁን የትኞቹ ትምህርት ቤቶች መልሶ ለማደራጀት ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባና በምን ምክንያትስ እንደሆነ ይከታተላል፣ እንዲሁም ዋናውን ስለ አደረጃጀት ሥልት ስለሚደረግ ውሳኔ ከተጨማሪ ሥራ ጋር ይህንን ትንተና ያመለከታል።

## ራእይ

የዲሲፒኤስ ዋና ትምህርታዊ እቅድ ሌላ ለእነዚህ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች አደረጃጀት ራእይ እንዲኖር የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል። የለውጡን ጉዳይ፣ በተማሪዎች አመዳደብ ፖሊሲ በክፍሎች አደረጃጀት፣ የመጋቢ ትምህርት ቤቶች አዝማሚያዎች እና የትምህርት ቤት መጠንን ቀጥሎ በተቀመጠው መልክ በጉልህ ይጠቅሳል፤



21st Century School Fund
Brookings Institute
District of Columbia Government
Urban Institute

> "የክፍሎች አደረጃጀትና የመገቢ ትምህርት ቤቶች ሁኔታ ከአንዱ የክፍል ደረጃ ወደ ሌላው የክፍል ደረጃ የሚደረገውን የተማሪዎችንና የወላጆቻቸውን ሽግግር እንዲያቃልለው አብረው የሚሠሩባቸውንና መልሰም እርስ በርሳቸው የሚሠሩ ስብስብ ትምህርት ቤቶችን ለወላጆች ለማቅረብ እንድንችል ትምህርት ቤቶችን በማደራጀት ረገድ የተሻሉ ሥራዎች መሥራት መቻል አለብን። ሥልታችን በተጨማሪ፣ ወላጆች በቤተሰብ አነስተኛ ጥረትና ስለ ወደፊቱም ሁኔታ ጥርጣሬና እርግጠኛ ያለመሆን ጉዳይ ሳይገጥመው ልጆቹ ሊማሩ የሚችሉበትን ትምህርት ቤት መምረጥ የሚያስችል የትምህርት ቤት ፖሊሲ እንዲኖር ያስችላል።"

በተጨማሪ፣ ዋናው የትምህርት እቅድ፣ የትምህርት ቤት አጎራባች ክልሎች እንዲለወጡ፣ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ፣ እና ትምህርት ቤቶች የሚቀበሏቸው ተማሪዎች ቁጥር ከፍ እንዲል ሀሳብ አቅርቧል። ዋናው የትምህርት እቅድ (MEP) የእነዚህ ለውጦች ሥራ ላይ መዋል ከታች የተመለከተውን የትምህርት ሥርዓት ይፈጥራል።

> "ቅልጥፍና ባለው ሁኔታ ቦታና መምህራን እንዲመደቡ የተደረገው ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ለመደገፍ፣ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው በትላልቅ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ጥቂት ተማሪዎች፣ ትምህርት ቤቱን ለማንቀሳቀስ ሲባል ብቻ በአነስተኛ ወጪ ጥቂቶች ያልተሟላ ትምህርት እየተሰጣቸው እንዳይበደሉ የሚደረግበት፣ የተሻለ አኳኋን ተመጣጥኖ የተደራጀ አጥጋቢ ትምህርት የሚገበይበት የትምህርት ቤት ሥራዓት ለመፍጠር።"

በዚህ ሠነድ ውስጥ ተመልክቶ የሚገኘው፣ በጥናታዊ ቡድኑ፣ ትምህርት ቤትን እንደገና ለማደራጀት፣ የተሰጠው የመፍትሔ ሀሳብ እርምጃዎች በዋናው የትምህርት እቅድ ላይ ባሉት ፓሊሲዎችና ሥልቶች ላይ በመመርኮዝ ነው። እነዚህ የመፍትሔ ሀሳቦች፣ ማኅበረሰቦቻቸውን መሠረት ያደረጉና እድሜአቸው ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለደረሱ ልጆች የደኅንነት ዋስትና ያላቸውና ከመኖሪያ ቤቶቻቸውም በተወሰነ የእግር ጉዞ ርቀት ላይ ለሚገኙ ለክልል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት መርሀ ግብርና አገልግሎቶች የሚሰጡ ናቸው። ይህ ራዕይ ዲሲፒኤስ ለለጋ የልጅነት ትምህርትና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የበለጠ ጠንካራ የአካዳሚክ ትምህርት ለመስጠትና ለእድሜ ተመጣጣኝ የሆነ የተማሪዎች አገልግሎትና እንዲሁም እድሜያቸው ለመካከለኛ ትምህርት ቤት የደረሱ ተማሪዎችን ትምህርት ለመደገፍ የዲሲፒኤስ የማያሰልስ ቁርጠኛነት የታከለበት ነው። የመካከለኛ ክፍሎች ትምህርት እየተጠናከረ ያለው በሕፃናት የወጣቶች Children's Youth Investment ሲሆን ከትምህርት ቀናት ውጪ በዲስትሪክቱ ለሚገኙና በመካከለኛ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ተማሪዎች በሙሉ ከፍተኛ ጥራት ባለው ተግባራዊ ክንውኖች እንዲገለገሉ እድል በመስጠት ነው። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ magnet እና በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ዲሲፒኤስ በአጥጋቢ የተማሪዎች ቁጥር ድጋፍ እና አገልግሎቶች በመደገፍ ተማሪዎች ሁሉ ለመመረቅ የሚያስፈልጓቸውን ትምህርቶች ሁሉ አጠናቀው ለኮሌጅ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ጤናማና ጠንካራ ሥራዓተ ትምህርት ለመፍጠር እየተለመ ነው።

## መልሶ ለማደራጀት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ትምህርት ቤቶችን መለየት

ትምህርት ቤትን መልሶ የማደራጀትና የአማራጮችን ጉዳይ በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃዎች ለማቅረብ አጥኚው ቡድን በክልል ትምህርት ቤቶችና በተማሪዎች የመመዝገብ ለውጦች ላይ ትንተና አድርጓል። ቡድኑ፣ በትምህርት ቤት ደረጃ፣ በተማሪዎች ደረጃ፣ እና እንዲሁም በክልል ደረጃ የመረጃዎችን ስብስብ አዘጋጅቶ አቅርቧል።

### ለመመዝገብ የማመልከት ማሽቆልቆል እና ከሚገባው ቁጥር በታች ተመዝግቦ የመገኘት ሁኒታዎች

በ 2002 - 2006 ባሉት ጊዜያት፣ ከ 5 - ዓመት የበለጠ የዲሲፒኤስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መካከለኛ ወይም አማካይ ለውጥ (21%) እና የምዝገባ መጠን ከዲሲፒኤስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከቅድመ ትምህርት - 5 (PS - ) ባሉ ክፍሎች የተማሪዎች አማካይ ቁጥር ከ (272) አንሶ የተገኘበትን ለመወሰን የዲሲፒኤስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ትንተና ተካሂዶባቸዋል። ከፍ ብሎ የነበረ የተማሪዎች የምዝገባ መጠን ከፍ ብሎ ይታይ ከነበረው ማሽቆልቆል ከጀመረ አንሥቶ እና በእያንዳንዱ የክልል ጣቢያም አጥጋቢ ቁጥር ያለው የተማሪዎች ተመዝግበው እንዲገኙ ያለው ፍላጎት እንደተጠበቀው ሆኖ ባለመገኘቱ ትምህርት ቤቶችን የመዝጋቱ ፍላጎት፣ አንድ ላይ ወደ ሌላ ክልል ለማዛወር ወይም ለማዋኻድና ለመቀላቀል፣ ቡድኑ ከእነዚህ ጣምራ ምክንያቶች ትምህርት ቤቶች በየትኛው ጫና እንደወደቀባቸው መርምሯል። እነዚህም ሁኔታዎች፣ የትኞቹ ትምህርት ቤቶች መልሶ ማደራጀት እንደሚሹ ለይቶ ለማወቅ የመጀመሪያው ቀዳሚ ደረጃ መስፈርት ሊሆኑ በቅተዋል።

እነዚህን የጋራ መመዘኛ መስፈርቶች ተግባር ላይ ማዋሉ፣ 33 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ፣ በጋራ ወደ ሌላ ክልል እንዲዛወሩ አለበለዚያም እንዲዋኻዱ ለማድረግ በቅቷል። ሁለት ከፍተኛ የካፒታል ወጪ የተደረገባቸው ትምህርት ቤቶች በመሠረቱ ሥራው እየተካሄደ ሲሆን እነዚህም ትምህርት ቤቶች HD Cooke እና Wheatley – እና ከወዲሁ የተዋኻደ አንድ ትምህርት ቤት –Adams – እነዚህ ባጠቃላይ ከዝርዝሩ ውስጥ ተሰርዘዋል።

ያው መስፈሪያ - ከአጋማሽ በላይ የምዝገባ መቀነስ እና ከአጋማሽ መጠን በታች የመቀነስ ሁኔታዎች በመካከለኛ ትምህርት ቤቶች ተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል። ለመካከለኛና ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመካከለኛው የ 5 ዓመት ለውጥ 29% አሽቆልቁሏል። ለመካከለኛና ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (9ኛ ክፍሎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሸጋገሩ ከመደረጉ በፊት) የምዝገባው መጠን 334 ተማሪዎች ነበር። እነዚህን ጥምር መስፈርቶች ሥራ ላይ የማዋሉ ሁኔታ የሰባት መካከለኛና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ሊያስገኝ ችሏል።

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደረጃ፣ የአመዘጋገብ ለውጥና መጠን ሁኔት ከአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተለየ ሁኔታ በ magnet ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርምሯል። አጋማሽ የ 5 - ዓመት የምዝገባ ለውጥ በ magnet ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደረጃ የ 7% ጭማሪና በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አጋማሽ የምዝገባ ለውጥ 14% ማሽቆልቆል አሳይቷል። የአጋማሽ የምዝገባ መጠን 418 እና 825 ነበር።

## ትምህርት ቤት በትምህርት ደረጃ ትንተና

የመጀመሪያው ደረጃ መስፈርት ሥራ ላይ የመዋል ሁኔታ ተጨማሪ ትንተና የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት ቤቶች ሊሰጥ ችሏል። የጥናቱ ቡድን፣ በተነጣጠሉ ትምህርት ቤቶች ላይ፣ የተማሪዎች ምዝገባ ከፍ ይላል ተብሎ በሚጠበቅባቸው ክልሎች፣ እና መልሶ ለማጠናከር ለታቀዱ 33 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ የተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት አዝማሚያን በሚመለከት ተጨማሪ ትንተናዎችን አካሂዷል። ከዲሲፒኤስ ሠራተኞች፣ ከትምህርት ምክትል ከንቲባው ጽሕፈት ቤት፣ ከስቴቱ የትምህርት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ጽሕፈት ቤት፣ እና ከእቅድ ጽሕፈት ቤት ከተውጣጡ ባለሞያዎች ጋር በተያያዘ ሁኔታ፣ የጥናቱ ቡድን ለሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት፣ የመጀመሪያውን የመስፈርት ደረጃ ያሟሉ ትምህርት ቤቶችን ለመጀመሪያ ተጨማሪ የሂደት ግምገማ ለማድረግ ስብሰባ አካሂዷል። እነዚህ የሥራ ስብሰባዎች የክልል እውቀትን ከመረጃ ጭብጦች ጋር፣ ካርታዎችና ከከተማው የእቅድ መረጃ ጋር በማቀናጀት፣ የተማሪዎችን የምዝገባ አዝማሚያዎችን የበለጠ ለመረዳት ተጠቅመውበታል። ምንም እንኳን የውይይቱ ወቀት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮሩ ቢሆኑም፣ ጥቂት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዚሁ ዓይነት የአጠናን አቀራረብ ዘዴዎች በመጠቀም እንዲጠኑ ተደርጓል።

የሚከተሉት የትምህርት ቤቶች እቅድ ጉዳዩች ተመርምረዋል፤

- ለብቻ ተገለው የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን ለይቶ ማውጣት - እነዚህም ከማንኛውም የዲሲፒኤስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ ½ ማይል ርቀው የሚገኙ፣ ወይም አንድ ትምህርት ቤት በመዘጋቱ የተነሣ ተማሪዎች ቅርብ ወደ ሆነው አማራጭ ትምህርት ቤት ለመድረስ ዋና የጅኦግራፊ ክልል ማቋረጥ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው።

  o *ምሳሌ፤* Kenilworth አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ሌላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመድረስ Interst-295 ማቋረጥ ሲኖርባቸው፣ በ Benning አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ ሌሎች አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ገብተው ለመማር የ Benning ን ጉዳናና የ East Capitol መንገድን ማቋረጥ አለባቸው።

- የተማሪዎች ቁጥር ያድጋል ተብለው የተያዙ ክልሎች ደግሞ፣ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ቁጥር ሊንሰራራ ይችላል ተብሎ በሚጠበቁ አካባቢዎች፣ በከተማይቱ በሙሉ እነዚህን የመሳሰሉ ትምህርት ቤቶችን ከመዘጋት ለመዳን እነዚሁ ተለይተው ታውቀዋል።

o *ምሳሌ፤* Draper አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአዲስ ቤቶች ግንባታ ሥራና ለመኖሪያ ክልሎች እቅድ በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት ይኸው የተጠቀሰው ትምህርት ቤት፣ ከፍተኛ ብዛት ያላቸው ልጆች የሚወለዱበትና ወደ ሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚገቡ በርካታ ልጆች ይኖራሉ ተብሎ በታቀደው ክልል ውስጥ ነው።

- ትምህርት ቤቶች ከነጭራሹ በሚዘጉበት ወቀት፣ ተማሪዎች እንዴት እንደሚሰባጠሩና "ተቀባይ" ትምህርት ቤቶችም በቂ ቦታ ይኖራቸው እንደሆነ ለማወቅ፣ በአሁኑ ወቅት በትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎች ብዛትና እንዲሁም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ክልል የመኖሪያ ቤቶችን ብዛት ከግምት በማስገባት ስለዚሁ ሁኔታ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል።

  o *ምሳሌ፤* በአሁኑ ወቅት በ Rudolph ክልል የሚገኙ የተማሪዎችን አመዘጋገብ ሁኔታና እንዲሁም በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል ማናቸውም ዐይነት መሰናክል ያለመኖሩን ከግ ምት በመውሰድ፣ Truesdell አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ Rudolph ለሚመጡ ተማሪ ዎች ተቀባይ ትምህርት ቤት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

- ትኩረት የተደረገባቸው ትምህርት ቤቶች የራሳቸው ሁኔታ - የሕንፃ መጠን፣ የጅምናዚየም መኖር፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ እና/ወይም የመጫወቻ ቦታ ከውጪ መኖር፣ - እና ትምህርት ቤቱና እን ዲሁም ለማኅበረሰቡ ተስማሚና ደስ የሚል የሪሶርስ ማዕከል ሆኖ የመገኘቱ፣ (ምሳሌ፣ የአቴሌቲክ መስኮች ወይም የመዝናኛ ማዕከል)።

  o *ምሳሌ፤* Scott Montgomery አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከ Kennedy የመዝናኛ ማዕ ከል ሁለት ብሎኮች ወይም መደዳዎች ያህል ቀረት ብሎ የሚገኘው አነስተኛ የሆነ የተወሰኑ የተተከሉ መቀመጫዎች አሉት።

የዲሲፒኤስ ካፒታል ፈንድ ለትምህርት ቤቶች ማመጣጠንና የትምህርት ቤቶች ፋሲሊቲዎችንም ከዚህ የማስ ተካከል ዙር በኃላ ዘመናዊ ለማድረግ፣ በአሁኑ ወቅት ያለው ሁኔታና የትምህርት ቤቶች ሕንጻዎች አጠቃቀም ሁኔታ እንደ አንድ ጉዳይ ከግምት አልተወሰደም ነበር።

## የሚያስከትለው ከተማ አቀፍ ሁኔታዎች

ይህ የትምህርት ቤቶች ጉዳይ ውይይት፣ ከተማይቱን በሙሉ በሚዳስስ የራእይ ውይይት ላይ የተንተራስ ነው። በትምህርት ቤቶች ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ በርካታ የመኖሪያ ክልል እና የመኖሪያ ቤቶች ፖሊሲ ጉዳ ዬች ተለይተው ታውቀው ነበር። ወላጆችን ከነልጆቻቸው የመሳብና ተረጋግተው እንዲቀመጡ የማድረግ የከተ ማይቱ የሆነውን ዋና ዐላማ ከግብ ለማድረስ በትምህርት ቤቶችና በመኖሪያ ክልል አገራባቾች መካከል ትብብር መኖር እጅግ ወሳኝና አስፈላጊም ነው። በዚህ ላይ ታሳቢ የሆኑ ጉዳዬች የሚከተሉትን ያካትታል።

- በተለይ ለቤተሰቦች፣ ቤቶች የማግኘት እድል፣
- የተለያዩ አዳዲስ የቤቶች ዐይነቶች የመገኘት ሁኔታ ተዛማጅነት (ይኸውም ኮንዶ፣ የተለያዩ ደረጃ ዎች ያሏቸው የኪራይ ቤቶች መኖር፣ የግል መኖሪያ ቤቶች) እና ልጆች ያሏቸውን ቤተሰቦች የሚያ ስተናግዱ መኖሪያዎች የመገኘት፣
- የትምህርት ቤትና የአጎራባች ክልል የመለዋወጫ ወቅት 4፣
  - o በተማሪዎች የምዝገባ ማነስ ምክንያት የሚዘጋ ከሆነና በአቅራቢያውም ለስዎች አቅም የሚመጥኑ የአዳዲስ ቤቶች በተከታታይ የመሠራትና በእነዚህም ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ልጆች የሚማሩት የት ነው?
- አጎራባቾች ለልጆች ሠላማዊና በቀላሉ የእግር ጉዞ የሚደርሱበት፣
- ለዋና የሕዝብ መጓጓዣና መመላለሻ አመቺነት ያላቸው ትምህርት ቤቶች መገኘት፣
- የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች የማያቋርጡ እድገት፣
- እንደ ዲሲፒኤስ ጠንካራ ፕሮግራሞችና ዘመናዊነት ያላቸው ወላጆችን ለሚማርኩ ፋሲሊ ቲዎች እድገት ግምት መኖር፣

## የማኅበረሰብ በሥራ መጠመድ እና የአፈጻጸም እቅድ

ከተማይቱ ትምህርት ቤቶችን እንደገና ለማደራጀት አንዴ የመጀመሪያ ዝርዝር ካወጣች በኋላ፣ የክልል ማኅበረሰብ አባላት ገንቢነት ባለው ሁኔታ ስለ እቅዱና ስለ ውሳኔዎቹ ሊወያዩበት የሚያስችል ሂደት መኖር አለበት።

እንዲህ ዐይነቱ ሁሉን ለማድረስ የሚችል ጥረት፣ የከተማይቱን የጥራት እቅድ እንደሚያሻሽለው በጣም አጥብቀን እናምናለን። በዚህ ወቅት፣ የከተማይቱ እና የትምህርት ቤት መሪዎች የሚከተሉትን በዝርዝር ለመንደፍ ዝግጁ ሆነው መገኘት አለባቸው።

1. ለምን ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እንደታቀደ፤ የክልል ለውጥ፣ የፕሮግራም መነሣት፣ ፕሮግራሞችን የማዋኻድ፤
2. እንደገና ትምህርት ቤቶችን ለማደራጀት ለምን እንደታቀደ፤ የምዝገባ መጠን እና ማሽቆልቆል፣ በትምህርት ቤት ሕንፃና በድርጅቱ በሙሉ መጠቀም አለመቻል፣ በአቅራቢያ ያሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች፤
3. ለተቀባይ ትምህርት ቤቶች ምን እንደታቀደ፤ ፕሮግራምና አግልግሎቶችን የማሻሻል፣ የክልል ትምህርት ቤቶችን እንደገና ማደራጀት፣ ካፒታልን ማሻሻል፣ የክፍል ደረጃዎችን ወይም የመጋቢዎችን ገጽታዎች ማሻሻል፤
4. ለመልሶ ማደራጀቱ ሊፈለግ ስለሚችለው የበጀት መጠን እንዴት እንደሆነ፣ የተወሰኑ ቋሚ ውጪዎች፣ እና ከተማሪዎችም ጋር የሚተላለፍ ፈንድ፣
5. መልሶ ማደራጀቱ መቼ እንደሚካሄድ፣
6. ጫናው በሚመለከታቸው ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች የት እንደሚመደቡ፤ ለወላጆች የሚቀርብላቸው የትምህርት ቤቶች አማራጮች ምን እንደሆኑ እና ሂደቱም እንዴት እንደሚያዝ፣ እና ያም ሂደት እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል፣

የዚህ፣ ትምህርት ቤቶችን መልሶ የማደራጀት አካል በመሆን የትኞቹ እንደ ሚዘጉ አንዴ ከተወሰነ፣ የሚዘጋው ትምህርት ቤት ሕንጻ ተመልሶ ለምን ተግባር ሊውል እንደሚችል የሚያሳይ በሁለተኛ ደረጃ የሚካሄድ ውሳኔ እንደገና መታየት አለበት።

## ዋቢ ሠነዶች

1) Background on need for reorganization: DCPS & charter school enrollment trends, DCPS facilities utilization (መልሶ ለማደራጀት መሠረቶች፤ የዲሲፒኤስ እና የቻርተር ትምህርት ቤቶች የምዝገባ አዝማሚያዎች፣ ዲሲፒኤስ የፋሲሊቲዎች አጠቃቀም)

2) Tables by level: ES, MS (including K-8s), SHS
Table of school enrollment & building capacity table, by level (ሠንጠረዦች በትምህርት ቤት ደረጃዎች፤ አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ K — 8ተኛ)፣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣
የትምህርት ምዝገባ ሠንጠረዦች እና የሕንፃዎች የመያዝ ችሎታ መጠን ሠንጠረዥ፣ በትምህርት ቤት ደረጃ)



21st Century School Fund
Brookings Institute
District of Columbia Government
Urban Institute